# ስለአበበ ገላው ካነሱት ...

## ዓለም ዘለዓለም ደስታ፣ ኅዳር 2009 ዓም

መቼም ነገርን ነገር ያነሳዋል ሆነ እና ነው እንጂ በአርዕስቱ ላይ ስለተጠቀሰው ሰውዬ ላነሳ እና ወይም የሳቸውን በሚመለከት ልፅፍ ቀርቶ ባለፉት ቦታ እንዳላልፍ አምላኬ አታገባጥመኝ፣ አታስተያየኝ ካልኩ ጊዜው ሰንብቷል። ወንድሜ ልጅ ኃይለኢየሱስ አዳሙ እኔም ስለ ሀገራችን ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ እና በተለይም ስለ ዐማራው ባለኝ እውቀት እና ግንዛቤ የምጽፈውን በጽሞና እንዲያነቡልኝ ነው። ይህንን በኃዛቤ ያለውን ሳካፍል እንደማይቀየሙኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ነገር ግን አብሮ ለመኖር፣ «ሰው አስቀይማለሁ» የሚሉ ሁኔታዎችን እንደ ባህላችን ወስደነው «ኧረ ነብዝ ይህ እኮ ስህተት ነው» የሚል ጠፍቷል። አሁን ለደረስንበት ጣጣ ከሰባት ሚሊዮን በላይ የሚሆን የዐማራ ሕዝብ የት እንደደረሰ የሚናገር የለም። «ለእውነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለፍትህ ቆምናል» የሚሉ መንግሥታት እና የሰብአዊ መብት ጠባቂዎች ሰምተው እንዳልሰሙ፣ ዐይተው እንዳላዩ ሆነዋል። መጀመሪያውኑ እንድንጠፋ ሌት ከቀን ያለሙልን መንግሥታት በጎ ያስቡልናል ብለን ያሰብን ቀን ሁኔታዎች መኮላሸታቸውን አለመገንዘባችን ነው።

በልጅነቴ አንድ በቅርብ የማውቀውን ታሪክ ላጫውትዎት። ታላቅ እህቴ እና ታላቅ ወንድሜ በአንድ ጉዳይ በቁጭት (በንዴት) ሲወያዩ እሰማ ነበር። ሁለቱም ያኔ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ይማሩ ነበር (ነፍሳቸውን ይማረውና)። እህቴ እና ወንድሜ በቁጭት ሲወያዩበት የነበረው ጉዳይ በዩኒቨርሲቲው ተማሪ ስለነበሩ የኤርትራ ተወላጆች ነው። የኤርትራ ተወላጆች መጻሕፍት ቤት ውስጥ የሚያጠኑ እና የሚያነቡ በመምሰል፣ ከመጻሕፍቱ ውስጥ ስለኢትዮጵያ ሀገራችን ጥሩ ጥሩ የተጻፈውን ገፅ እየቀደዱ ታሪክ ሲያበላሹ ወንድሜ ይመለከታል። ይህንንም ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ «ለምን ይህ ይደረጋል» በማለት ጭቅጭቅ ይነሳና ነገሩ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዘዳንት ጋር ይደርሳል። በኋላም መጻሕፍቱን እየገነጣጠሉ ያበላሹት ምንም ነገር ሳይደርስባቸው ትምሕርታቸውን እንዲቀጥሉ እንደተደረጉ ሰምቻለሁ። ነገር ግን ወንድሜ እና ጓደኞቹ ዩኒቨርሲቲው ፕሬዘዳንት ጋር ተጠርተው «ሁኔታው እስከዚህ ድረስ የሚያደርስ አልነበረም። መጽሐፍ የተቀደደ አይመስለንም። የእናንተ ችግር በጣም ደመ-ግንፍል ናችሁ። ሁለተኛ ይህ ነገር እንዳይደገም።» ተብለው «ለዛሬው በይቅርታ አልፈናችኋል» ተብለው ከቢሮአቸው አሰናበቷቸው። ስለዚህ ወንድሜ ልጅ ሄኖክ የሺጥላ የተናገረው ወይም በመጣጥፍ ያቀረበው ከእውነት የራቀ አይደለም።

ትልቁ ቁም ነገር፣ ከ40 ሚሊዮን በላይ የሆነውን የዐማራውን ሕዝብ ጉዳይ እየፈተላችሁ እና እየቋጫችሁ ስለሆነ፣ ጊዜያችሁን ባልተሻማሁ ነበር። ስለዚህ ጉዳዩን ያላለፍኩት «ይቺ ባቄላ ካደረች

አትቆረጠምም» እየሆነብኝ ተቸግሬ ነው። ይህ ባይሆንብኝ ኖሮ ይህንን ጽሑፍ ለመጻፍ አልነሳም ነበር። በእኔ ሚዛን ዐማራ ሆነው ዐማራውን ለከዱት ወይም ለሚዶልቱበት ሰዎች ጥላቻዬ ወሰን የለውም።

ልጅ ኃይለኢየሱስ፥ አቶ አበበ ገላው ብቻ ሳይሆኑ የዐማራ ተወላጆች ዐማራ በመሆናቸው አፍረው፣ ተሸማቀው፣ ነፃነት ባለባቸው ሀገሮች ሁሉ የሚኖሩ ብዙ አሉ። ስማቸው ወደፊት ኢትዮጵያ ነፃነቷ ሲመለስ ለዐማራው ሕዝብ እንደሚቀርብ ጥርጥር የለኝምም። «ዐማራ በሆንኩ» የሚሉበት ቀን ግን ሩቅ አይደለም። ብቻ እኛ የተጋጋለውን የአርበኝነት ትግል እናፋፍም፤ የቀረው እዳው ገብስ ነው።

ኢሣት የሚባለውን TV እና ሬድዮ፣ በተለይም «የኤርትራ ድምፅ ነው» ተብሎ የሚታማውን ድርጅት፣ አቶ አበበ ገላው እንደሚመሩት ይነገራል። ከሳቸውም ጋር ለሆዳቸው ያደሩ በጣት የሚቆጠሩ የዐማራ ተወላጆች እንዳሉ ይታወቃል። ነገር ግን ዐማራው ከተወለደበት፣ ከኖረበት እና ከከበረበት ሥፍራ ሲፈናቀል፣ ሲገደል፣ ክብሩ ሲደፈር፣ «ዐማራ» ማለት አሳፍሯቸው «ዐማርኛ ተናጋሪው» እያሉ ቱልቱላቸውን ሲነፉ ሰምተን ታዝበናል። አንዳንዴም ዐማራው ግፊት ሲያሳድረባቸው፣ በስልክም፣ በጽሑፍም ሲጨቀጨቃቸው፣ የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ሊቀመንበርን ለይስሙላ ያህል ለቃለ መጠይቅ ሲያቀርቧቸው ዐይተናል። እንደ ፋሲል የኔዓለም ዓይነቶቹ ደግሞ ከጋዜጠኛ ሙያ ባፈነገጠ አቀራረብ የሞረሽን ሊቀመንበር ሲያንጓጥጡ አዳምጠናል። ይቺን ያህል መድረክ የተገኘው በዓለም ላይ በሚገኙ ዐማሮች ግፊት፣ በተለይም በአውስትራሊያ በሚኖሩ ዐማሮች ጭቅጨቃ ነው። ኢሣት ውስጥ ያሉት ጋዜጠኞች ለዐማራው ሕዝብ ደንታ የማይሰጣቸው መሆኑን እስከ ዛሬ ድረስ ያልተረዳ የዐማራ ተወላጅ ካለ እርሱ ተጃጅሎ የቀረነውንም እኛንም ሊያጃጅለን እሽሩሩ የሚለን ነው።

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ባይኖር ኖሮ፣ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ያቀጣጠሉት የዐማራው ጉዳይ ተቀብሮ በቀረ ነበር። ልጅ ሄኖክ የሺጥላ የሚመሰገን፣ ልናከብረው የሚገባ፣ ከዐማራው አብራክ የተገኘ ወጣት ነው። ስለዚህ «ትግሉ ወደ ዋናው ቁም ነገር ማትኮር አለበት» የተባለው እኔም የምጋራው ቅዱስ ኃሣብ መሆኑን ተቀብያለሁ። ሆኖም ቀረ ይህ ጉዳይ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ዐማራውን ለእዚህ ለደረሰበት ሰቆቃ እና ስቃይ፣ ለኢትዮጵያ መፈራረስ፣ በዐማራው ሕዝብ ላይ እልቂት (Genocide) እንዲፈጸምበት፣ የመጀመሪያውን የጥፋት መሠረት የጣለው ዋለልኝ መኮንን እኮ ዐማራ ነው። አልፎም ተርፎ «ዐማራው ኢትዮጵያን የብሔር እና የብሔረሰቦች እስር ቤት አድርጓታል» ብሎ ባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ የጻፈውን መጽሐፍ ኤርትራውያኖች ወደ አማርኛ ተርጉመውለት በስሙ እንዲበተን ያደረገ ከሃዲ ባንዳ ነው። በእርሱ ጽሑፍ የኤርትራ፣ የትግራይ እና የኦሮሞ ተገንጣዮች ብዙ ተጠቅመውበታል። ስለሆነም ዋለልኝ መኮንንን ኢትዮጵያ ለዚህ ለደረሰችበት ሁኔታ ታሪክ ምንጊዜም በመጥፎ ሲያነሳው ይኖራል፤ እኔም ነፍሱን አይማረው እላለሁ።

ልጅ ኃይለኢየሱስ፦ ዐማራውን እና ኢትዮጵያን ለማጥፋት ባለፈው ስድሣ ዓመት የተቀነባበረውን ለታሪክ ባለሙያዎች ልተወው። ለእርስዎም ለማስረዳት እንዳልሞከር ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች እንዳይሆንብኝ በመፍራት ትቼዋለሁ። እርስዎ እና እኔ ልንስማማበት እንችላለን ብየ እንደማስበው፣ በውጭ ጠላቶቻችን ላይ አትኩረን የራሳችንን ጠላቶች እየረሳናቸው ነው። ታላቁ መሪያችን ፕሮፌሠር አሥራት ወልደየስ ነፍሳቸውን ይማረውና፣ «ያስቸገረን ሆዳም ዐማራው ነው» እንዳሉት፣ «ዐማርኛ ተናጋሪ» እያሉ ጥቃታችንን የሚያደበዝዙት ከእኛው ከዐማራው አብራክ የወጡት ናቸው። ስለዚህ የሌላው አይግረመን፤ ሊገርመንም አይገባም። ከእነሱ አንድ እርምጃ ተራምደን መገኘት የነበረብን እኛ ነበርን። እነሱ ግን ቀበቷችንን በደንብ ሳንታጠቅ አገኙን፤ አጠቁን፣ ገደሉን፣ ቀበሩን። ነገር ግን ያልገባቸው የዐማራ ሕዝብ እንደ ሰንበሌጥ መሆኑን ነው። ሰንበሌጥ የመጣበትን አውሎ ነፋስ ለጥ ብሎ ያሳልፋል፤ ነፋሱም ከቆመ በኋላ ቀጥ ብሎ ይቆማል። ስለሆነም እኒህ ጠላቶች ዐማራው እንደዚያ መሆኑን ሊረዱ የሚገባቸው ጊዜው የደረሰ ይመስለኛል።

ሩጫው ለምን ይምስልዎታል? ዐማራው አንድ ላይ ከሆነ ከራሱ ተርፎ ለመላው ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪቃ ሕዝብ ለውጥ እንደሚያመጣ ስለሚታወቅ ነው። ስለዚህ ዐማራውን ለመከፋፈል ሤራ የሚያሸርቡት የዐማራ ሃቀኛ ልጆች አይደሉም። እንዲያውም ይህ የወያኔ እጅ ብቻ ሳይሆን የውጭ ሀገርም እጅ እንዳለበት አልጠራጠርም። በጣም የሚያሳዝነው እና አንጀት የሚያበግነው የወልቃይት የዐማራ ማንነት ጥያቄ፣ በአቋራጭ ተጠልፎ፣ ሸክም የማይከብደው የፈረደበት የጎንደር ሕዝብ፣ በስሙ ገንዘብ ሲለመንበት፣ የዐማራው ልሂቃን «ይህ ነውር ነው፤ ዐማራውን አትለዩት» ብሎ የሚናገር መጥፋቱ፤ «አይ እማማ ኢትዮጵያ የወላድ መሀን ሆንሽ!» ያሰኛል። ዛሬ እማማ ኢትዮጵያ ህልውናዋ ደብዝዞ፣ አንድነቷ ተናግቶ፣ ተቆራርሳ፣ ተሸጣ፣ የባንዳ ልጆች መጨፈሪያ ብቻ ሳትሆን የዜጎቿን ሙብት የሚያስከብር ጠፍቶ፣ የማንም መፈንጫ ሆናለች።

ኢትዮጵያን ዓለም ከተፈጠረችበት ከ7558 ዓመታት ጀምሮ አምላክ ጠብቆ አቆይቷታል። በዚህ ረጅም ዘመን ከሁሉም ማኅበረሰብ ጋር ተጋብቶ፣ ተዋልዶ ከኖረበት ሀገር እየተለቀመ እንደ ፋሲካ በግ እየታረደ፣ ከራሱ አብራክ የወጡ ዐማሮች ሲያደሙት ማየት በጣም ያስቆጣል። የዐማራው ልሂቃን የዐማራውን ሕዝብ እና ኢትዮጵያን የካዱት ለምን ይሆን? ይኸንን ለሥነ-ልቡና ባለሙያዎች ልተወው።

የወልቃይት (ጎንደር) ሕዝብ ጥያቄ የዐማራው የማንነት ጥያቄ ነው። የወልቃይት ዐማራ ያቀጣጠለው የበጋ እሳት ወደ ጎጃም፣ ወደ ሸዋ፣ ወደ ወሎ ወዘተርፈ ተላልፎ እያየን ነው። በጣም የሚገርመው ይኸንን የዐማራ ሕዝብ ትግል ጠልፈው ለመውሰድ እና ስሙን ለመቀየር የሚጥሩ፣ ከዐማራው አብራክ የወጡ አንዳንድ ለሆዳቸው ያደሩ ዐማሮች ለመሆናቸው ጭልጭልታ እየታየ ነው። ዋናው ዓላማቸው የዐማራውን

ትግል ለማኮላሸት እና ዐማራውን ለስድስተኛ ጊዜ ህልውናውን ሊያደበዝዙት እየተወራጩ ይገኛሉ። እነዚህ ግለሰቦች እና ቡድኖች የዐማራውን ትግል የገንዘብ ማካበቻ እያደረጉት ነው።

የዐማራው ትግል በኢትዮጵያ ውስጥ ጎልቶ እያለ እዚህ አሜሪካ ውስጥ ለምን «የጎንደር ኅብረት» «የጎጃም ህብረት» ፣ «የሸዋ ኅብረት» የሚባሉ ድርጅቶች ማቋቋም አስፈለገ? በቅርቡም «የወሎ ህዝብ ኅብረት» የሚባል እንደሚቋቋሙ አልጠራጠርም። የዐማራ ሕዝብ ኅብረት እንደማቋቋም በተናጥል በጠቅላይ ግዛት ደረጃ ማቋቋም ለምን አስፈለገ? ይህ ሁሉ «የወልቃይት ጥያቄ የዐማራ የማንነት ጥያቄ ነው» ብሎ የተነሳውን ሕዝብ ለመከፋፈል ነው። ለ25 ዓመታት «ዐማራው ምን ነካው?» ስንል እንዳልነበረ፣ ዛሬ የተመኘነው እና የጸለይንለት ደርሶ፣ ዐማራው ተደራጅቶ ለወገን፣ ለሀገር ተገን ሆኖ በሞላው ዐማራ ከሚኖርበት አካባቢ አልፎ ለኢትዮጵያ ሻማውን እያበራ ነው።

ባለፉት አራት ዓመታት ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት በዐማራው ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ እና ግፍ ለዓለም ሕዝብ አሳውቋል። ከሁሉም በላይ ዐማራውን ለማነቃቃት ሌት ተቀን ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ፣ የግል ጉዳያቸውን እና ቤተሰባቸውን አግልለው፣ ለመላው ዐማራ ሕዝብ ሸንጣቸውን ገትረው ጠበቃ፣ መምህር ሆነው ለታገሉት ዐማራ ወገኖቼ ከመቀመጫዬ ሰባት ጊዜ ብድግ ብዬ እጅ እነሳለሁ። «የዐማራው ንቅናቄ የእናንተው ውጤት ነው» ስል ዐማራ በመሆኔ ኩራት ይሰማኛል።

ልጅ ኃይለኢየሱስ አዳሙ፡- በመጨረሻ በጣም ከማከብራቸው፣ ከምወዳቸውና በአካል አግኝቻቸው ከማላውቃቸው ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ «ማንነት መሬት ላይ አይዘራም» በሚል ርዕስ ከጻፉት መጣጥፍ ጠቅሼ ልለይዎት ነው።

« ... አማሮች ጎሠኝነትን የሚቃወሙት ጎጠኝነት የአንድን ሀገር ሕዝብ ስለሚለያይ፣ በጠላትነት ስለሚያጠፋጥፐ፣ ጎሠኝነት እና ዲሞክራሲ የማይታረቁ ሥርዓቶች ስለሆኑ ነው። ንጉሣዊውን ሥርዓት ለመጣል የታገሉት የአማራ ልጆች የዲሞክራሲን ሥርዓት ለማስፈን ነበር። የደርግን ሥርዓት ለመገርሰስ ደማቸውን ያፈሰሱት የአማራ ልጆች የዲሞክራሲን ሥርዓት ለማስፈን ነበር። የአማራ ልጆች አሁንም የሚታገሉት የጥንቱን ዓላማቸውን አንግበው ነው። የአማራ ልጆች ኢትዮጵያ ነፃ ሳትወጣ፣ በሀገራቸው ላይ የዲሞክራሲ ሥርዓት ሳይሰፍን እንቅልፍ አይወስዳቸውም። አደራ፣ አደራ የዐማራ ልጆች የወጠንነውን ግብ ሳናደርስ እንቅልፍ እንዳይወስደን።»

ቸር ይግጠመን።

ዓለም ዘለዓለም ደስታ